**<u>በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ</u>**

**<u>የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመዘርዘር</u>**

**<u>የወጣ አዋጅ (ረቂቅ) ቁጥር-------/2013 ዓ.ም</u>**

**<u>መግቢያ</u>**

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የሚወከሉበት የፌዴሬሽን ምክር ቤት እንደ አንድ ሕገ መንግሥታዊ ተቋም የሕጎች ሁሉ የበላይ በሆነው በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት የተቋቋመ በመሆኑና ሥልጣንና ተግባሩ ጠቅለል ባለ መልክ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ፤

የፌደሬሽን ምክር ቤት ተልዕኮውን በተሟላ መንገድ መፈጸሙ የሕገ መንግሥት የበላይነት፣ ሕገ-መንግስታዊነት፣ ዘላቂ ሰላም፣ ዋስትና ያለው ዲሞክራሲ ለማረጋገጥ፤ እንዲሁም አንድ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመገንባት ያለው አስተዋጽኦ የጎላ በመሆኑ፣

ከፌደሬሽን ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር ጋር በተያያዘ በጊዜ ሒደት በአፈጻጸም የታዩ የሕግና የአሰራር ክፍተቶችን መለየትና ማሻሻያ ማድረግ በማስፈለጉ፣

በጥቅል የተቀመጡት ኃላፊነቶችም ለአፈጻጸም ያመች ዘንድ በአዋጅ ዘርዘር ብለው እንዲደነገጉ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ</u>**

**1. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመዘርዘር ተሻሽሎ የወጣ አዋጅ ቁጥር....../2013" ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣-

1. "ሕገመንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት ነው፡፡
2. "ምክር ቤት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው፡፡
3. "ሕግ" ማለት በፌዴራሉ ወይም በክልል ሕግ አውጪ አካላት የሚወጡ አዋጆች እና የፌዴራልና የክልል የመንግሥት አካላት የሚያወጧቸው ደንቦችና መመሪያዎች ሲሆኑ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችንም ያካትታል፡፡
4. "የከተማ አስተዳደሮች" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ናቸው፡፡
5. "አፈጉባዔ" እና "ምክትል አፈጉባዔ" ማለት የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባዔና ምክትል አፈጉባዔ ናቸው፡፡
6. "ቋሚ ኮሚቴ" ማለት ከምክር ቤት አባላት መካከል የሚመረጡ አባላትን የያዘ ሆኖ ከምክር ቤቱ የሚመራለትን ጉዳይ መርምሮ የዉሳኔ ሃሳብ ለምክር ቤቱ የሚያቀርብ ኮሚቴ ነው::
7. "አስተባባሪ ኮሚቴ" ማለት የምክር ቤቱ አፈጉባኤ፣ ምክትል አፈጉባኤ፣ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች እና በምክር ቤቱ በቋሚነት የሚሰሩ የቋሚ ኮሚቴ ጸሐፊዎች እና ያለድምጽ ቃለ ጉባኤ በመያዝ የምክር ቤቱ ጽ/ቤት ኃላፊ የሚሳተፉበት ኮሚቴ ማለት ነው፡፡
8. "ጊዜያዊ ኮሚቴ" ማለት በምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች ወይም በአስተባባሪ ኮሚቴ ሊሰሩ የማይችሉ፣ አስቸኳይ እና አስፈላጊ ስራዎችን ለመከወን በምክር ቤቱ ለተወሰነ ጊዜ የሚቋቋም ኮሚቴ ነው::
9. "ብሔር ብሔረሰብ ሕዝብ" ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው ሊግባቡ የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልከዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው፡፡
10. "ማሕበረሰብ" ማለት ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ለመሆን በፌዴሬሽን ምክር ቤት እውቅና ያልተሰጣቸው ነገር ግን እውቅና እንዲሰጣቸው በሕገ መንግሥቱ መሰረት ጥያቄ የሚያቀርቡ ናቸው፡፡
11. 11· "የሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ" ማለት በሕገመንግስቱ አንቀጽ 82 መሰረት የተቋቋመው የፌዴራሉ የሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ነው፡፡
12. "ፍርድ ቤት" ማለት በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሲሆን ሌሎች በሕግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጣቸውን አካላትም ይጨምራል፡፡
13. "የመንግስት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ" ማለት በማናቸውም ደረጃ የሚገኝ የመንግስት አካል ወይም ባለሥልጣን የሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ነው፡፡

14. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው::
15. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋመ ክልል ማለት ነው፣

**3. <u>የፆታ አገላለፅ</u>**

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

**4. <u>የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. ሕገ መንግሥንት ይተረጉማል፣ሕገ መንግስታዊ ክርክር ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሰጣል፣
2. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔን ያደራጃል፣
3. የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብትን በተመለከተ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ በሕገመንግሥቱ መሠረት ይወስናል፣
4. በሕገ መንግሥቱ የተደነገገው የሕዝቦች እኩልነትና በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር ያደርጋል፣
5. በክልሎች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሔ ይፈልጋል፣
6. የክልሎችና የፌዴራል መንግሥት የጋራ ተብለው የተመደቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈሉበትን እንዲሁም የፌዴራል መንግስት ለክልሎች ድጎማ የሚሰጥበትን ቀመር ይወስናል፣
7. 7· በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን ይለያል፣
8. ማንኛውም ክልል የፌዴራል ሕገ መንግሥቱን በመጣስ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ የፌዴራል መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ ያዛል፣
9. በሕገ መንግሥት አንቀጽ 103 (5) መሠረት የምርጫ ቦርድ በሚያቀርብለት ረቂቅ መሰረት የምርጫ ክልሎች አከላለልን ይወስናል፣
10. የሕዝብ ብዛታቸው አነስተኛ በመሆኑ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተለየ ውክልና የሚያስፈልጋቸው ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነት እና ቁጥር አስቀድሞ በሚዘጋጅ ግልጽ መስፈርት መሰረት ይወስናል፤
11. በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 99 መሠረት ለፌዴራል ወይም ለክልል መንግሥታት ተለይተው ባልተሰጡ ታክስና ግብር የመጣል ሥልጣኖች ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በጋራ ይወስናል፣
12. በማንኛውም ክልል ሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱና ክልሉ ድርጊቱን ማስቆም ሳይችል ሲቀር ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመሆን ለክልሉ ምክር ቤት መመሪያ ይሰጣል፣
13. የፌደሬሽን ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሶስት አባላትን መርጦ ይወከላል፣

14. በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 70(2) መሰረት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በሚደረግ የጋራ ስብሰባ የአገሪቱን ፕሬዝዳንት ይመርጣል፣
15. በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 104 እና 105 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) በተደነገገው መሠረት ሕገ መንግሥቱን በማሻሻል ሂደት ይሳተፋል፣
16. በሥልጣኑ ሥር በሚካተቱ ጉዳዮች ላይ ከሌሎች ጋር በመተባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና እንዲሰጥ እንዲሁም ጥናት እና ምርምር እንዲካሔድ ያደርጋል፣
17. የምክር ቤቱን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፣
18. የራሱን አፈጉባዔና ምክትል አፈጉባዔ ይመርጣል፣
19. የራሱን የስራ አፈጻጸምና የውስጥ አስተዳደር ደንብ ያወጣል፣

## ክፍል ሁለት

## ሕገ መንግስትን ስለ መተርጎም

### 5. መሠረቱ

1. የሕገመንግሥታዊ ክርክር ጉዳይ ሲነሳ በምክር ቤቱ ውሳኔ ያገኛል፡፡
2. ምክር ቤቱ ሕገ መንግስቱን በመተርጎም ሒደት ማናቸውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ የመንግስት አካል ወይም የባለሥልጣን ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን ሆኖ ሲያገኘው ተፈጻሚ እንዳይሆን ይወስናል፡፡
3. ምክር ቤቱ በሕገ መንግሥት ትርጉም የምክር አገልግሎት ለመስጠት አይገደድም፡፡

### 6. ለሕገ መንግስት ትርጉም ስለሚቀርቡ ጉዳዮች

የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው፣

1. በሕገ መንግስቱ ውስጥ ለመንግስት አካላት ወይም ሌሎች ተቋማት በተሰጡት ስልጣን፣ ተግባራትና ኃላፊነቶች ይዘትና ዳራ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ፣
2. በፌዴራሉ መንግስትም ሆነ በክልል ሕግ አውጪ አካላት የሚወጡ ሕጎች ከሕገ መንግስቱ ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ ሲነሳና ጉዳዩ በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለ ጉዳዩ ሲቀርብ፣
3. በማናቸውም የመንግስት አካል ወይም የባለሥልጣን የመጨረሻ ውሳኔ በሕገ መንግስቱ የተደነገጉት መሰረታዊ መብቶቹና ነጻነቶቹ ተጥሰዋል በሚል ጥያቄ ለማቅረብ መብት ባለው ሰው አቤቱታ ሲቀርብ፤
4. በፌዴራል የመንግስት አካላት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች ሲቀርብ፤
5. በፌዴራል መንግስቱ እና በክልል መንግስታት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች ሲኖሩ፤
6. በክልሎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች ሲኖሩ፤

7. በፍርድ ቤት ሊወሰን በማይችል በማናቸውም ሕገ መንግስታዊ ጉዳይ ላይ በፌዴራል ወይም በክልል ሕግ አውጪ ምክር ቤት አንድ ሶስተኛ አባላት ወይም በፌዴራልም ሆነ በክልል አስፈጻሚ አካላት ጥያቄ ሲቀርብ፣
8. የፌደራል መንግስት የሚያወጣቸው ሕጎች በክልሎች ስለሚፈጸሙበት ሁኔታ አለመግባባት ሲፈጠርና ጥያቄውም በሚመለከተው አካል ሲቀርብ፣
9. የፌደራል ወይም የክልል መንግስት ህጎችና ፖሊሲዎች በህገ መንግስቱ ውስጥ በተደነገጉት መርሆዎችና አላማዎች ላይ የተመሰረቱ አይደሉም የሚል ክርክር በክልል መንግስት፣ በፌደራል መንግስት፣ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አንድ ሶስተኛ አባላት ወይም የክልል ምክር ቤት አንድ ሶስተኛ አባላት ሲቀርብ፣
10. የክልል ሕገ መንግስት ተርጓሚ አካል የፌደራል ሕገ መንግስትን በመተርጎም ሂደት ቀደም ሲል በፌደሬሽን ምክር ቤት ወይም በሌላ ክልል ሕገ መንግስት ተርጓሚ አካል በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ከተሰጠ የሕገ መንግስት ተርጉም የተለየ ውሳኔ ባሰበ የክልል ሕገ መንግስት ተርጓሚ አካል በሚቀርብ ጥያቄ፣

## 7. <u>የሕገ መንግስት ትርጉም  ስለ መስጠት</u>

1. ምክር ቤቱ የሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ሕገ መንግሥቱን መተርጎም ያስፈልጋል በማለት በጉዳዩ ላይ የሚያቀርበውን የውሳኔ ሃሣብ መርምሮ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል፡፡
2. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልግም በማለት ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኙን ለምክር ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ይግባኝ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## 8. <u>ስለ ይርጋ</u>

1. በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ መሰረት በአጣሪ ጉባኤው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በተሰጠ በመቶ ሰማንያ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለምክር ቤቱ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም፡-

   ሀ. በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 28 በስብዕና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በተመለከተ እና፤

   ለ. የብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ሙብቶች ወይም የስልጣን ክፍፍል እና መሰል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የይግባኝ  አቤቱታዎች የማቅረቢያ ጊዜ በይርጋ አይታገድም፡፡

## 9. <u>የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ማቅረብ ስለሚችሉ ሰዎች</u>

1. የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው፣

ሀ. በባለ ጉዳዩ ወይም በህጋዊ ወኪሉ

ለ. በሚመለከተው ፍርድ ቤት፣ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት

ሐ. የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በሚወክል ማህበር ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች በሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል ነው::

2. ለምክር ቤቱ የሚቀርቡ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄዎች አቀራረብ ዝርዝር በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## 10. ስለ ክፍያ

1. ለምክር ቤቱ የሚቀርብ የሕገመንግሥት ትርጉም ጥያቄ ከክፍያ ነፃ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ቢኖርም እንደአስፈላጊነቱ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ መሰረት አቤቱታ አቅራቢው ክፍያ እንዲፈጽም ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 11. ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ስለ መላክ

ምክር ቤቱ በቀጥታ የሚቀርብለትን አዲስ የሕገመንግሥት ትርጉም ጥያቄ ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው ይልካል፡፡

## 12. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው ስለ ሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ

1. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው ሕገ መንግስቱን መተርጎም ያስፈልጋል ብሎ ሲያምን የውሳኔ ሀሳቡን በአፋጣኝ ከበቂ ሕገ መንግስታዊ ማብራሪያ እና ሙሉ ሰነዶች እና መረጃዎች ጋር ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ ከሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ እንደደረሰው ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ይመራል፡፡
3. የውሳኔ ሀሳቡ የተመራለት ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩን በመመርመር የደረሰበትን የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ ጉባኤ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አጣሪ ጉባኤው በሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ወይም በምክር ቤቱ ጉባኤ ማብራሪያ እንዲሰጥ በተጠየቀ ጊዜ ቀርቦ ማብራሪያ መስጠት ይኖርበታል፡፡
5. ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ባልሰጠበት ወይም እየታየ ባለ ጉዳይ ላይ ማናቸውም አካል በሚዲያ በጉዳዩ ላይ መግለጫ መስጠት ወይም ማሳተም ወይም በማህበራዊ ሚዲያ መልቀቅ የተከለከለ ነው፡፡ ይህ ለጥናትና ምርምር የሚደረግን ህትመት አይጨምርም:: ይህ ክልከላ ለጥናትና ምርምር የሚደረግን ህትመት አይጨምርም::

## 13. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ስለሚያቀርበው የስራ አፈጻጸም ሪፖርት

የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ስለስራው ክንውን ለምክር ቤቱ ጉባኤ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## 14. በሕገ መንግሥት ትርጉም ተፈፃሚ ስለሚሆኑ መርሆዎች

ምክር ቤቱ የሚቀርቡለትን የሕገመንግሥት የትርጉም ጉዳዮች መርምሮ ለመወሰን በሌሎች አገራት አቻ ተቋማት እንዲሁም ኢትዮጵያ አባል ባጸደቀቻቸው አለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት ህግጋት አተረጓጎም ስራ ላይ የዋሉ የሕገመንግሥት ወይም የሕገ መንግስታዊ መብቶች አተረጓጎም መርሆዎች በሥራ ላይ ማዋል ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይሸፈናል::

## 15. ተጨማሪ ማስረጃ ወይም አስተያየት ስለ ማሰባሰብ

1. ምክር ቤቱ በሕገ መንግሥት ትርጉም የመጨረሻ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲሰባሰብ ወይም ከሚመለከተው አካል ማስረጃ እንዲቀርብ ወይም አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ተቋማት ባለሙያዎች ቀርበው እንዲያስረዱ ሊያዝ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያቀርብ ወይም ቀርቦ እንዲያስረዳ በምክር ቤቱ የታዘዘ አካል ምክር ቤቱ በወሰነው ቀን ማስረጃውን ማቅረብ ወይም ቀርቦ ማስረዳት ይኖርበታል፡፡
3. በምክር ቤቱ ማስረጃ እንዲያቀርብ የታዘዘ አካል በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያለበቂ ምክንያት ማስረጃውን ያላቀረበ እንደሆነ አግባብነት ባላቸው ሕጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡
4. አንድ ለምክር ቤቱ የቀረበ የህገ መንግስት ትርጉም ጉዳይ ሰፋ ያለ የህዝብን ጥቅም የሚመለከት ወይም መሰረታዊ የግል ወይም የጋራ መብቶችን ሚመለከት ከሆነ የምክር ቤቱ አጋር (አሚከስ ኩሪ) አመልካች በመሆን በግራ ቀኙ ክርክር ለማቅረብ የሚጠይቁ ተቋማትን ወይም ባለሞያዎችን ሊያስተናግድ ይችላል፤ በራሱ ተነሳሽነትም ሊጋብዝ ይችላል፡፡
5. ምክርቤቱ በሕገ መንግሥት ትርጉም የመጨረሻ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ባለጉዳዮች ቀርበው አስተያየት እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 16. ሕገ መንግሥታዊነትን ስለ ሚያስረዳ አካል

1. የአንድ ሕግ ሕገ መንግሥታዊነት አከራካሪ ሆኖ ሲገኝ የማስረዳት ግዴታ የሚጣለው እንደነገሩ ሁኔታ የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥቱን በሕግ ጉዳዮች የማማከር ሥልጣንና ተግባር በተሰጠው የመንግሥት አካል ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አከራካሪ ሆኖ የተገኘውን ሕግ ወይም ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊነት እንዲያስረዳ አግባብነት ያለው የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥታዊ አካል ምክር ቤቱ በሚወስነው ቀን ቀርቦ እንዲያስረዳ ሊታዘዝ ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት የአንድን ሕግ ሕገ መንግስታዊነት ወይም ውሳኔ እንዲያስረዳ የታዘዘ የመንግስት አካል ትዕዛዙ ደርሶት በተወሰነው ቀን ቀርቦ ያላስረዳ እንደሆነ ምክር ቤቱ የቀረበለትን ጉዳይ መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ከተገለፀው በተጨማሪ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት እንዳስፈላጊነቱ ጉዳዩን ከያዘው ፍርድ ቤት ሙሉ የመዝገብ ግልባጭ መጠየቅ ወይም ባለጉዳዩን ወይም ሌላውን ተከራካሪ ወገን ማነጋገር ይችላል፡፡

**17. <u>ሕገ መንግሥታዊ አይደለም ስለተባለ ሕግ</u>**

የአንድ ሕግ አካል ድንጋጌ ሕገ መንግሥታዊ አይደለም የሚል ውሣኔ የተሰጠበት እንደሆነ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በቀር ውጤቱ ተወስኖ የሚቀረው በዚያው ድንጋጌ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

**18. <u>ጉዳዩን በአጭር ጊዜ ውስጥ ስለመወሰን</u>**

ምክር ቤቱ ከአጣሪ ጉባኤው የቀረበለትን ጉዳይ መርምሮ በተቻለ ፍጥነት ውሣኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**19. <u>ስለ እግድ</u>**

የፌደሬሽን ምክር ቤት በቀረበለት የህገ መንግሰት ክርክር ጉዳይ በአመልካቹ ላይ ሊተካ የማይችል ጉዳት ይደርሳል ወይም ሁከትና ብጥብጥ ሊከሰት ይችላል ወይም ሌላ ከባድ አሳማኝ ምክንያት አለ ብሎ የሚያምን ከሆነ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ይህንኑ አስመልክቶ ማመልከቻ ጥያቄ ሲቀርብለት የጉዳዩ አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በአፈጉባኤው ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤የእግድ ውሳኔውን ከመስጠቱ በፊት ግራ ቀኙን ሊሰማ ይችላል፡፡

**20. <u>የውሳኔ ይዘት</u>**

1. የምክር ቤቱ የሕገመንግስት ትርጉም ውሣኔ የጉዳዩን ዝርዝር መግለጫ፣ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልጋል ወይም አያስፈልግም ያለበትን ምክንያትና የደረሰበትን መደምደሚያ በግልጽ የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፡፡
2. የምክር ቤቱ የሕገመንግስት ትርጉም ውሣኔ እና የአጣሪ ጉባኤው የውሳኔ ሃሳብ ግልጽ እና ጥራቱን የጠበቀ መሆን ይኖርበታል፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡
3. በሕገ መንግስት ትርጉም ላይ ምክር ቤቱ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ጥያቄውን ላቀረበው እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡
4. ማናቸውም ባለጉዳይ ወይም የመንግስት አካል የምክር ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ተዘጋጅቶ በአስር ቀናት ጊዜ ውስጥ ሊሰጠው ይገባል፡፡

**21. <u>የሕገ መንግሥት ትርጉም ውሣኔ ተፈጻሚ መሆን ስለሚጀምርበት ጊዜ</u>**

1. በሕገ መንግሥት ትርጉም ላይ ምክር ቤቱ በሚሰጠው ውሣኔ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር ተፈፃሚ የሚሆነው ውሣኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡
2. አንድ ሕግ ወይም የአንድ ሕግ አካል ድንጋጌ ወይም የመንግስት አካል ወይም የባለሥልጣን ውሳኔ ወይም ልማዳዊ አሰራር ተፈጻሚ እንዳይሆን በምክር ቤቱ ሲወሰን ውሳኔው ከአስር ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለሚመለከተው አካል መድረስ ይኖርበታል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ቢኖርም አንድ ሕግ ሕገመንግሥታዊ አይደለም ተብሎ የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ሕጉን ላወጣው የፌዴራል ወይም የክልል የመንግሥት አካል በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ሕጉን እንዲያሻሽል፣ እንዲለውጥ ወይም እንዲሰርዝ መገለጽ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተገለጸው ሕግ ስለመሻሻሉ፣ ስለመለወጡ ወይም ስለመሰረዙ ምክር ቤቱ ክትትል ያደርጋል፡፡

**22. <u>የሕገመንግሥት ትርጉም ውሣኔ ውጤት</u>**

1. በሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ላይ ምክር ቤቱ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ አስገዳጅ ይሆናል፡፡
2. ውሣኔው በሁሉም ዘንድ እንዲታወቅ በሚዲያና ምክር ቤቱ ለዚሁ ዓላማ በሚያዘጋጀው ልዩ መጽሔት ታትሞ ይወጣል፡፡
3. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በፌዴራል የስራ ቋንቋ፣ በክልል የስራ ቋንቋዎች እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ይታተማል፡፡

**23. <u>የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት</u>**

1. ምክር ቤቱ ከሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሚቀርቡ የውሳኔ ሃሳቦችና በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በይግባኝ የሚመጡ ጉዳዮችን እየመረመረ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ ከአባላቱ የተውጣጣ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፡፡
2. ኮሚቴው በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በይግባኝ የቀረበ ጉዳይ ለምክር ቤቱ ጉባኤ መቅረብ ይገባዋል፣ ወይም አይገባውም በማለት እንዲወስን ውክልና ሊሰጠው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን በተመለከተ የሚነሱ ጥያቄዎችን ስለማስተናገድ</u>

**24. <u>መሠረቱ</u>**

1. የፌዴሬሽን ምክር ቤት የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን በተመለከተ በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡
2. ማንኛውም ማህበረሰብ ማንነቴ አልታወቀልኝም፤ ቋንቋዬን፣ ባህሌን እና ታሪኬን የማሳድግበት ሁኔታ አልተመቻቸልኝም የሚል አቤቱታ ሲያቀርብ ጥናት እንዲካሄድ ያደርጋል፤ የውሳኔ ሃሳብ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤
3. ማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ የራስ በራስ ማስተዳደር መብቴ ተሸራርፏል፤ ቋንቋዬን፣ ባህሌን እና ታሪኬን የማሳድግበት ሁኔታ አልተመቻቸልኝም፣ በአጠቃላይ በፌዴራል ሕገመንግሥት የተደነገገው መብቴ አልተከበረም ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት አድሎ ተፈጽሞብኛል የሚል አቤቱታ ሲቀርብ ጥናት እንዲካሄድ ያደርጋል፤ የውሳኔ ሃሳብ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 በተመለከቱ ጉዳዮች ለክልሎች የሚቀርቡ አቤቱታዎች በግልባጭ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት መቅረብ አለባቸው፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጥያቄው ስለመቅረቡ ለሚመለከተው የክልል ምክር ቤት ያሳውቃል፡፡

## 25. ክልል ለማቋቋም ስለሚቀርብ ጥያቄ

1. የማንኛውም ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ክልል የመመስረት ጥያቄ፣

ሀ. የክልል መመስረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም በሕዝብ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥና ጥያቄው በጽሑፍ ለክልሉ ምክር ቤት ሲቀርብ፣

ለ. ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክር ቤት ጥያቄው በደረሰው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለተጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ህዝበ ውሣኔ ሲያደራጅ፣

ሐ. ክልል የመመስረት ጥያቄው በብሔሩ በብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ ሕዝበ ውሣኔ በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍ፣

መ. የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣኑን ለጠየቀው ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሲያስረክብ፣

ሠ. በሕዝበ ውሣኔ የሚፈጠረው አዲስ ክልል ጥያቄ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል ሲሆን በሥራ ላይ ይውላል ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክልል የመመስረት ጥያቄ አልተፈፀመልኝም ወይም በተሰጠው ውሣኔ ቅሬታ አለኝ የሚል ወገን ጥያቄውን ለምክር ቤቱ ማቅረብ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው ጥያቄ ለምክር ቤቱ የሚቀርበው በጽሁፍ ሆኖ የክልል ምሥረታ ጥያቄ ባቀረበው የብሔረሰብ ምክር ቤት ይሆናል፡፡
4. ምክር ቤቱ በዚህ መልኩ በቀረቡለት ጉዳዮች ላይ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**26. መገንጠልን በተመለከተ ስለሚቀርብ ጥያቄ**

1. ምክር ቤቱ የመገንጠል ጥያቄው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39(4)(ሀ) መሠረት በብሔር ብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ ምክር ቤት ሕግ አውጭ አካል ሁለት ሦስተኛ ድምፅ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ እና ጥያቄው በጽሑፍ ሲቀርብለት፡-

   ሀ. የብሔር ብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ ምክር ቤት ሕግ አውጭ ውሣኔ በደረሰው በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠየቀው ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሣኔ ያደራጃል፣

   ለ. የመገንጠሉ ጥያቄ በሕዝበ ውሣኔ በአብላጫ ድምፅ መደገፉን ሲያረጋግጥ ለብሔር፣ ብሔረሰቡ፣ሕዝቡ ምክር ቤት ሥልጣን ያስረክባል፡፡

   ሐ. በሕግ በሚወሰነው መሠረት የንብረት ክፍፍል ያደርጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የሚካሔደውን ሕዝበ ውሳኔ ለማስፈፀም ምክር ቤቱ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድን ሊወክል ይችላል፡፡

**27. የክልል መፍትሔን አሟጦ የመጨረስ ግዴታ**

1. በአንቀጽ 24 የተመለከተው ጥያቄ ወደ ምክር ቤቱ የሚቀርበው በክልሉ በሚገኙት የተለያዩ የመስተዳድር እርከኖች ቀርቦ አጥጋቢ መፍትሔ ያልተሰጠው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡
2. ክልሎች በአንቀጽ 24 የተመለከቱት ጥያቄዎች ሲቀርቡላቸው በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ይወስናሉ፡፡ ዝርዝሩን ክልሎች በሚያወጡት ህግ ሊወስኑ ይችላሉ::
3. የቀረበው ጥያቄ በክልሉ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ካልተሰጠው ወይም በተሰጠው ውሣኔ ቅሬታ አለኝ የሚል ወገን ጉዳዩን ለምክር ቤቱ በቀጥታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**28. ስለ ጥያቄ አቀራረብ**

1. የማንነትና ራስን በራስ የማስተዳደር መብቶችን አስመልክቶ ለምክር ቤቱ የሚቀርብ ጥያቄ በጽሑፍ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. የሚቀርበው ጽሁፍ የጥያቄውን ይዘት በዝርዝር የሚያሳይና ጥያቄው የነዋሪው ሕዝብ ወይም የብሔር፣ ብሔረሰቡ መሆኑን ለማመልከት እንደ አስፈላጊነቱ ከነዋሪው ወይም ከማህበረሰቡ አባላት ቢያንስ አምስት ከመቶ የስም ዝርዝር

ፊርማና አድራሻ የያዘ ወይም እንዳስፈላጊነቱ ጥያቄ ባቀረበው የመስተዳድር አካል ባለሥልጣን የተፈረመና ማህተም ያረፈበት መሆን ይገባዋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለምክር ቤቱ ጥያቄ ለማቅረብ የሚመጣ ግለሰብ ወይም ግለሰቦች ከጠያቂው ማህበረሰብ የተወከሉ ለመሆናቸው በቂ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት ወይም አለባቸው፡፡ ዝርዝሩ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**29. <u>የፌደሬሽን ምክር ቤት ስለሚወስዳቸው እርምጃዎች</u>**

1. በሕገ መንግስቱ መሰረት የማንነት እና የራስ በራስ ማስተዳደር ጥያቄ ለምክር ቤቱ ሲቀርብ ምክር ቤቱ በሕገ መንግስቱ መስፈርቶች ማለትም፣

   ሀ. ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው ስለመሆኑ፣

   ለ. ሊግባቡ የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው ስለመሆኑ፣

   ሐ. የጋራ የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ ስለመሆናቸው

   መ. የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልከዓ ምድር የሚኖሩ መሆናቸውን እንዲረጋገጥ ያደርጋል፡፡

2. 2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተዘረዘሩት መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡
3. 3. ምክር ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከቱት መስፈርቶች መሰረት ስለሚወስንበት ሂደት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**30. <u>የሕዝቡን ፍላጎት ስለማረጋገጥ</u>**

1. በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 39(5) የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ የሕዝቡ ፍላጎት በሕዝበ ውሣኔ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፡፡
2. የሕዝብን ፍላጎት ለማረጋገጥ የሚከናወን ሕዝበ ውሣኔ የምርጫ ሕግን መሠረታዊ መርሆዎች በመከተል ይካሄዳል፡፡
3. የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕዝበ ውሣኔውን ለማስፈፀም ብሔራዊ የምርጫ ቦርድን ሊወክል ይችላል፡፡

**31. <u>ውሣኔ ስለ መስጠት</u>**

1. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሚያደርገው ጥናት እና በሕዝበ ውሳኔው ውጤት መሰረት የማንነት እና የራስን በራስ ማስተዳደር መብት ለጠያቂው ማህበረሰብ እንዲፈቀድ የወሰነ እንደሆነ የሚመለከተው ክልል በውሳኔው መሰረት እንዲፈጽም አስፈላጊውን ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡
2. የፌዴሬሽን ምክር ቤት የቀረበው የማንነትና የራስን በራስ ማስተዳደር ጥያቄ በሕገ መንግስቱ የተቀመጡትን መስፈርቶች አላሟላም ብሎ በወሰነ ጊዜ ለጠያቂው ማህበረሰብ ውሳኔውን ያሳውቃል፡፡
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 26 (1 እና 2) መሰረት ከብሔር፣ ብሔረሰብ ሕዝብ መብቶች ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሲቀርቡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጥናት በማድረግ እና የጥያቄውን አግባብነት በማረጋገጥ የጠያቂው ብሔር፣ብሔረሰብና ሕዝብ መብት እንዲከበር ውሳኔ ይሰጣል፡፡ በሚመለከተው የመንግስት አካልም እንዲፈጸም ያዛል፡፡ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡
4. ምክር ቤቱ በአንቀጽ 26 (1 እና 2) መሰረት የቀረበለትን ጥያቄ ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

**32. ጉዳዮችን በስምምነት ስለ መጨረስ**

በዚህ ሕገ መንግስት በተመለከተው መሰረት ከአንድ ማህበረሰብ ወይም ብሔር፣ብሔረሰብና ሕዝብ ሕገ መንግስታዊ የመብት ጥያቄ ቀርቦ በምክር ቤቱ በሚታይበት ጊዜ ጠያቂው ወገን እና ጥያቄው የተነሳበት ክልል ለጥያቄው ዕልባት ለመስጠት የተስማሙ እንደሆነ ምክር ቤቱ የስምምነቱን አግባብነት እና ሕጋዊነት መርምሮ ያጸድቃል፡፡ በስምምነቱ መሰረትም እንዲፈጸም በጽሁፍ ያስታውቃል፡፡

## ክፍል አራት

## አለመግባባቶችን ስለመፍታት

**33. መሠረቱ**

የፌዴሬሽን ምክር ቤት በክልሎች መካከል ወይም በፌዴራል መንግሥትና በክልል መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሔ ይፈልጋል፡፡

**34. ለውይይት ዝግጁ የመሆን ግዴታ**

1. ከፌዴራል መንግሥት ወይም ከሌላ ክልል ጋር የሚያወዛግብ ጉዳይ አለኝ ብሎ የሚያምን ወገን ከሌላው ጋር በዚሁ ጉዳይ ለመወያየት ያለውን ፍላጎት የሚገልጽ የጽሑፍ ጥሪ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

2. ጥሪው የደረሰው አካል በቅን ልቦናና በተቻለ ፍጥነት ቢረዝም በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለውይይት ዝግጁ መሆኑን ለጥያቄ አቅራቢው ወገን እና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
3. ሁለቱም ወገኖች ጉዳዩን በመቀራረብ ለመፍታት ፍቃዳቸውን የገለጹ ሲሆን ምክር ቤቱ ውይይቱ ፍሬያማ እንዲሆን አስፈላጊውን እገዛ ሁሉ ያደርጋል፡፡ ሂደቱንም በቅርብ ይከታተላል፡፡

**35. <u>ጥያቄውን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ስለማቅረብ</u>**

1. በአንዱ ወገን በቀረበው ጥያቄ ሌላኛው ወገን ለመወያየት ፈቃደኛ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ወይም የተጀመረው ውይይት መልካም ውጤት ካላስገኘ ጉዳዩ በአንዱ ወይም በሁለቱም ወገኖች አመልካችነት በምክር ቤቱ ሊታይ ይችላል፡፡
2. ምክር ቤቱ ጥያቄው እንደቀረበለት እንደነገሩ ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ለጊዜው የሚበጅ የመፍትሔ እርምጃ ሊወስድ ወይም እንዲወስድ ሊያደርግ ይችላል፡፡
3. ሁለቱም ወገኖች ጉዳዩን በመቀራረብ ለመፍታት ውይይት ካልጀመሩ ወይንም በሁለቱ ወገኖች ወይም በአንዱ ወገን አመልካችነት ጉዳዩን አስመልክቶ መፍትሔ እንዲሰጠው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ካላሳወቀ ምክር ቤቱ በራሱ አነሳሽነት አለመግባባቱን ለመፍታት የመፍትሔ እርምጃ ሊወስድ ወይም እንዲወስድ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**36. <u>የምክር ቤቱ እርምጃዎች ቅደም ተከተል</u>**

1. ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት

ሀ. እንደ አስፈላጊነቱ ባለጉዳዮቹ ውይይት የሚጀምሩበትን ወይም የሚቀጥሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ለ. አለመግባባቱ በውይይት ካልተፈታ የአለመግባባት መንስኤ የሆኑትን ጭብጦችን ይለያል፣

ሐ. በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የጽሑፍ አስተያየታቸውን አሉን ከሚሏቸው ማስረጃዎች ጋር እንዲያቀርቡ ያደርጋል፡፡

2. ምክር ቤቱ እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ወይም ጥናት በማድረግ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚመለከተው የመንግስት አካል ውሳኔውን እንዲያስፈጽም እና ሪፖርት እንዲያቀርብ መመሪያ ይሰጣል፡፡

**37. <u>የአስተዳደር ወሰን ውዝግብን ስለ መፍታት</u>**

1. የቀረበው ጥያቄ የአስተዳደር ወሰን ውዝግብን የሚመለከት ከሆነ ምክር ቤቱ የሕዝብን አሰፋፈርና ፍላጎት መሰረት በማድረግ ይወስናል፡፡
2. ምክር ቤቱ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 48 በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሰረት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**38. <u>የሕዝብ ፍላጎት እና አሰፋፈር</u>**

1. ምክር ቤቱ የሕዝቡን አሰፋፈር በማጥናት አካባቢው ወደ የትኛው ክልል መካለል እንዳለበት ለመወሰን የሚያስችል በቂ መረጃ እንዳለው ካመነ በዚያው መሠረት ይወስናል፡፡
2. ምክር ቤቱ የሕዝቡን አሰፋፈር በማጥናት አከራካሪው አካባቢ ወዴት መካለል እንዳለበት ለመወሰን የማይቻል መሆኑን ካመነ የሕዝቡን ፍላጎት መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

**39. <u>የሕዝቡን ፍላጎት ስለማረጋገጥ</u>**

1. የሕዝብ ፍላጎት በምስጢር ድምፅ አሰጣጥ በሚከናወን ሕዝበ ውሣኔ ይረጋገጣል፡፡
2. የሕዝብን ፍላጎት ለማረጋገጥ የሚከናወን ሕዝበ ውሣኔ የምርጫ ሕግን መሠረታዊ መርሆዎች በመከተል ይካሄዳል፡፡
3. የአስተዳደር ወሰን ውዝግብ የሕዝብን ፍላጎት ለማረጋገጥ የሚጠራ ሕዝበ ውሣኔ በቀበሌ ደረጃ ይከናወናል፡፡ የቀበሌው ስፋት ወይም ወሰን በተከራካሪ ወገኖች ስምምነት ካልተደረሰበት ምክርቤቱ በጥናት ላይ ተመስርቶ ይወስናል፡፡
4. ምክር ቤቱ ሕዝበ ውሣኔውን ለማስፈፀም ብሔራዊ የምርጫ ቦርድን ሊወክል ይችላል፡፡
5. የሕዝበ ውሣኔውን ውጤት መሠረት በማድረግ አወዛጋቢ የሆነው አካባቢ ከድምፅ ሰጪው ሕዝብ አብዛኛው ድምፅ ወደ ሰጠበት ክልል እንዲካለል ይደረጋል:: ሆኖም የሕዝበ ውሣኔው ውጤት አንዳንድ አካባቢዎችን በኪስ መሬትነት የሚያስቀር ከሆነ አወዛጋቢ የሆነው አከባቢ ሕዝቦች ባሉበት ክልል ሙብታቸው የሚከበርበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡
6. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በኪስ መሬትነት በቀረ አካባቢ ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች የቀሩበት ክልል፡-

   ሀ. በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 39(2) ላይ የተዘረዘሩትና ለክልሉ ነዋሪዎች የተረጋገጡ ሙብቶችን የማክበርና የማስከበር፣

   ለ. መሰረተ-ልማት ፍላጎቶችንና ማሕበራዊ አገልግሎቶችን ለማሟላት የሚያስችል በጀት የመመደብ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

7. የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከሕዝበ ውሳኔ እና ከመካለል በኋላ የሰላም ግንባታ ሥራዎችን የሚመለከታቸውን የመንግስት አካላት በማሳተፍ ያከናውናል፡፡

**40. ድምፅ የመስጠት መብት**

1. አግባብነት ያላቸው የምርጫ ሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ አወዛጋቢ በሆነው ቦታ በነዋሪነት የተመዘገበና እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ ድምፅ የመስጠት መብት ይኖረዋል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይወሰናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም አካባቢውን ለመልቀቅ የተገደደው በአስተዳደር ወሰን ውዝግቡ ምክንያት በተከሰተ የሕዝብ መፈናቀል መሆኑ ከተረጋገጠ ከአካባቢው የለቀቀ ቢሆንም ድምፅ ከመስጠት አይታገድም፡፡

**41. የአስተዳደር ወሰን ስለ ማካለል**

1. የሕዝበ ውሳኔው ውጤት ከታወቀ በኋላ የወሰን ማካለሉ ተግባር በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ተከናውኖ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ምክር ቤቱ በሕዝበ ውሳኔው መሰረት ውሳኔውን የሚያስፈፅሙ አካላትን በመለየት ያዟል::
2. የሚመለከተው የመንግስት አካል ከላይ ንዑስ አንቀጽ 1 በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔውን አስፈጽሞ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፡፡
3. በየደረጃው የሚገኙ የክልል እና የፌዴራል መንግስት አካላት ለአስተዳደር ወሰን ማካለሉ ሒደት አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲሁም ምክር ቤቱ አፈጻጸሙን የመከታተል ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

**42. ከሕዝበ ውሳኔ በኋላ ስለሚከናወኑ ተግባራት**

የሕዝቡን ፍላጎት ለማረጋገጥ ሕዝበ ውሳኔ ከተደረገ እና ውጤቱም ከታወቀ በኋላ የወሰን ውዝግቡ በተፈጠረባቸው አካባቢዎች የሰላም ግንባታ፣ የጋራ የልማት ስራዎች እና መልካም የሕዝቦች የርስ በርስ ግንኙነት እንዲኖር የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሰራል፡፡

**43. የጊዜ ገደብ**

ምክር ቤቱ የቀረበለትን የአስተዳደር ወሰን ጥያቄ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

**44. ሌሎች አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት ሁኔታ**

1. ምክር ቤቱ ከአስተዳደር ወሰን ውዝግብ ውጭ አለመግባባቶች ሲከሰቱ በጉዳዩ ያልተግባቡ ወገኖች ችግራቸውን በሰላምና በውይይት እንዲፈቱት ይጠይቃል፡፡ ሊያግባባቸውም ይጥራል፡፡
2. አለመግባባቱን በውይይት ሊፈቱ ካልቻሉ ምክር ቤቱ እንዳስፈላጊነቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ሥርዓት በመዘርጋት ለአለመግባባቱ መፍትሔ ይፈልጋል፡፡
3. የሕገመንግሥቱ የሥልጣን ክፍፍል መርህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ በፌዴራል መንግሥቱና በክልሎች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች ምክር ቤቱ መፍትሔ ይሰጣል፡፡

## 45. <u>የግጭት መከላከል እና ማስወገጃ ስልት ስለ መዘርጋት</u>

1. ምክር ቤቱ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለማስወገድ የሚረዱ ባህላዊም ሆነ ዘመናዊ የግጭት መከላከያና ማስወገጃ ስልቶችን በማጥናትና ከክልሎች ጋር በመቀናጀት የአሰራር ሥርዓትና ስልት ይዘረጋል፡፡ ተቋማዊ ይዘትና አደረጃጀት እንዲኖራቸውም ያደርጋል፡፡
2. የፌደሬሽን ምክር ቤት ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የግጭት መከላከያና ማስወገጃ ስልቶችን ለመዘርጋት ያስችለው ዘንድ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት አስፈላጊ እና ወቅታዊ መረጃዎችን መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ስለድጎማና የጋራ ገቢዎች ክፍፍል ቀመር አወሳሰን</u>

## 46. <u>መሠረቱ</u>

1. ምክር ቤቱ የክልሎችና የፌዴራሉ መንግሥት የጋራ ተብለው የተመደቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈሉበትን፤ እንዲሁም የፌዴራሉ መንግሥት ለክልሎች ድጐማ የሚሰጥበት ቀመር ይወስናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ስር የተጠቀሰው ቢኖርም ምክር ቤቱ የሚያዘጋጀው ቀመር ተጨባጭነትና ተቀባይነት ያለው በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ መሆን ይጠበቅበታል::

## <u>47. የቀመር ዓይነቶች</u>

1. ምክር ቤቱ በሕገ መንግሥቱ መሰረት ለክልሎች የሚሰጠው ድጎማ ቀመር የሚያዘጋጀው ጥቅል ዓላማ ያለው ወይም ውስን ዓላማ ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
2. ምክር ቤቱ የክልሎችና የፌዴራሉ መንግሥት የጋራ ተብለው የተመደቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈሉበትን ቀመር ያዘጋጃል፡፡

## 48. የድጎማ ዓላማዎች

1. ጥቅል ዓላማ ያለው ድጎማ በአጠቃቀሙ ላይ ቅድመ ሁኔታ የማይቀመጥበት እና ክልሎች ከራሳቸው ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ቅድሚያ ለሚሰጡት ጉዳይ እንዲጠቀሙበት የሚፈቅድ የድጎማ ዓይነት ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ስር የተጠቀሰው ድጎማ አይነተኛ ዓላማ ክልሎች በሕገ መንግሥቱ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ተቀራራቢ መንግሥታዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚያበቃ የፊስካል አቅም እንዲኖራቸው ማስቻል ይሆናል፡፡
3. ውስን ዓላማ ያለው ወይም በአላማ የተገደበ ድጎማ አንድ የተወሰነ ወይም የተለየ ዓላማን ለማሳካት ታስቦ በፌዴራል መንግሥቱ ለክልሎች የሚሰጥ የድጎማ ዓይነት ነው፡፡

## 49. የቀመር ዝግጅት አጠቃላይ መርሆዎች

1. የድጎማ በጀት ቀመር ዝግጅት መርሆዎች የክልሎችን የበጀት አጠቃቀም ነፃነት የሚያከብር፣ ገቢ አሰባሰብንና ውጤታማ የበጀት አጠቃቀምን የሚያበረታታ፣ ተተንባይ፣ ግልጽ፣ አሳታፊ፣ በቀላሉ ለመረዳት የሚቻል እና በተጨባጭ፣ አስተማማኝና ወቅታዊ መረጃዎች ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡
2. የድጎማ ቀመር ዝግጅት ዓላማዎች፣ ዝርዝር መርሆዎች፣ መስፈርቶች እና የመረጃ ምንጮች አግባብነት ባለው ሕግ ይወሰናል፡፡

## 50. በድጎማ እና በጋራ ገቢዎች ክፍፍል ስለሚኖረው ቅንጅት

1. የፌዴራል ድጎማና የጋራ ገቢዎች ክፍፍል ዓላማቸውን ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንዲቀናጁ ማድረግ ያስፈልጋል፤
2. ጥቅል ዓላማ ያላቸው እና ውስን ዓላማ ያላቸው ድጎማዎች ዓላማቸውን ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንዲቀናጁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 51. ስለ መረጃ

1. ለቀመር ዝግጅቱ በግብዓትነት የሚያገለግሉ መረጃዎች ወቅታዊና አስተማማኝ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
2. ለቀመር ዝግጅቱ በጥቅም ላይ የሚውሉት ማናቸውም ዓይነት መረጃዎች በዋነኝነት ከፌደራሉ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የሚመነጩ ናቸው፡፡
3. ከዚህ በላይ በንኡስ አንቀጽ (2) ስር የተጠቀሰው ድንጋጌ ቢኖርም ከሚመለከታቸው የፌዴራል ተቋማት እና ከክልል መንግሥታት ምንጮች የሚገኙ መረጃዎች አስተማማኝ ሆነው ከተገኙ ለቀመር ዝግጅቱ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡
4. ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው የፌዴራልና የክልል አስፈፃሚ አካላትና ሌሎች መረጃ አመንጪ ተቋማት ለቀመር ዝግጅቱ አስፈላጊ ሆነው የተገኙ መረጃዎችን በማቅረብ ረገድ የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

5. ይህ አዋጅ በሚጠይቀው መሰረት ለቀመሩ ዝግጅት የሚያስፈልጉትን መረጃዎች በወቅቱና በጥራት የማቅረብ ግዴታውን ያልተወጣ ማንኛውም ሰው በመገናኛ-ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 52. ስለ ክትትል እና ሪፖርት

የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ድጎማውና የጋራ ገቢ ክፍፍሉ በቀመሩ መሠረት መፈጸሙን ይከታተላል፡፡ ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡

## ክፍል ስድስት

## በሕዝቦች መካከል እኩልነትና አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር ስለማድረግ

## 53. መሠረቱ

በሕገ መንግሥቱ የተደነገገው የሕዝቦች እኩልነትና በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር ያደርጋል፡፡

## 54. የመሰረተ ልማት ሥርጭት ፍትሃዊነት ስለማረጋገጥ

1. በክልሎች መካከል የተመጣጠነ እድገት ለማምጣት የፌዴራል የመሰረተ ልማት አውታሮች ሥርጭት ፍትሐዊ መሆናቸውን ይከታተላል፡፡
2. የፌዴራል የመሰረተ ልማት አውታሮች ሥርጭት ፍትሐዊነት የሚለካው አስቀድሞ በተለዩ መስፈርቶችና መግባባት በተደረሰባቸው መለኪያዎች መሰረት ይሆናል፡፡
3. የሚመለከታቸው ተቋማት የመሰረተ ልማት ሥርጭት ፍትሐዊነትን አስመልክቶ የአፈጻጸም ሪፖርት ለምክር ቤቱ ያቀርባሉ፡፡
4. በንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው ቢኖርም ምክር ቤቱ ክልላዊ የመሰረተ ልማት ስርጭቶችን በየጊዜው በመከታተል ወቅታዊ ግብረመልስ ለሚመለከተው ተቋም ይሰጣል፡፡
5. ምክር ቤቱ በክልሎች የፌዴራል የመሰረተ ልማት አውታሮች ሥርጭት ፍትሐዊነት የጎደለው መሆኑን ሲያምን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና ለሚመለከታቸው ተቋማት ያሳውቃል፡፡
6. በንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት ግብረመልስ የተሰጠው የፌዴራል የመሰረተ ልማት ተቋም አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ለምክር ቤቱ ማሳወቅ አለበት፡፡
7. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለተቋማቱ የተሰጣቸውን አስተያየቶችና ግብረመልሶች ስለመካተታቸው እና የማስተካከያ እርምጃዎች ስለመወሰዳቸው ይከታተላል፡፡
8. ምክር ቤቱ የፌዴራል የመሰረተ ልማት ተቋማት እና ክልሎች የሚያካትት ብሔራዊ የጋራ የምክክር መድረክ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

9. የፌዴራል የመሰረተ ልማት አውታሮች ፍትሃዊ ሥርጭት እና የክትትል አግባብ ዝርዝር ምክር ቤቱ በሚዘረጋው የአሰራር ስርዓት ይወሰናል፡፡

**55. የሕዝቦችን እኩልነት እና አንድነትን ስለማዳበር**

1. ምክር ቤቱ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመሆን የሕዝቡን ዲሞክራሲያዊ ባሕል እና ንቃተ ሕገመንግሥት ለማዳበር የሚያስችል ስልት ይዘረጋል፤ ይከታተላል፤
2. በየደረጃው ያሉት የትምህርት ተቋሞች በሕዝቦች መካከል እኩልነትና አንድነትን የሚያጠናክሩ የትምህርት ዓይነቶች በሥርዓተ ትምህርታቸው ማካተታቸውን ምክር ቤቱ ይከታተላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ለተመለከተው ዓላማ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን በቂ ሽፋንና አምድ መመደባቸውን ይከታተላል፡፡
4. ለሕዝቦች እኩልነትና አንድነት መጠናከር እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ አመለካከቶችና አዝማሚያዎች እንዲጠኑና እንዲለዩ በማድረግ የመፍትሔ አቅጣጫ ቀይሶ የሚመለከታቸው ሁሉ እንዲያስፈጽሚቸው ያደርጋል፡፡
5. በአገራዊ ማንነት እና በብሔር ማንነት መካከል ሚዛን ለመጠበቅ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
6. ለህብረ-ብሔራዊ አገራዊ አንድነት የሚረዱ ጉዳዮችን ይለያል::
7. ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር ሚና ካላቸው አካላት ጋር ይሰራል::
8. ለአገራዊ አንድነት በሚጠቅም መልኩ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በፌዴራል ተቋማት ዉስጥ ሚዛናዊ ውክልና እንዲኖራቸው ይሰራል::
9. አካታች የሆነ የፌደራል የፖለቲካ ባህል እንዲዳብር የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
10. ልሳነ ብዝሃነት እንዲዳብር የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
11. በብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝቦች መካከል የመቻቻልና ለጋራ ዓላማ የመሥራት ባሕል እንዲዳብር እንዲሁም አንድነታቸው እንዲጠናከር የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፤
12. ምክር ቤቱ በክልሎች መካከል ያለው ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት እንዲጠናከርና በሕዝቦች መካከል እኩልነትና አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር፣-

    ሀ. ክልሎች በየዓመቱ የሚመደብላቸውን በጀት በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችላቸውን አቅም እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

    ለ. ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ልማትን ለማፋጠንና በክልሎች መካከል የተመጣጠነ እድገት ለማምጣት የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

    ሐ. በፌዴራሉ ሕገመንግሥት የሰፈሩትን የመንግሥት አወቃቀርና የሥልጣን ክፍፍል መሠረት በማድረግ ክልሎች የሚረዱበትንና በጋራ ለጋራ ጥቅም የሚሰሩበትን መድረኮች እና ሁኔታዎች ያመቻቻል እየተጠናከሩ እንዲሄዱም ድጋፍ ይሰጣል፤

13. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 የተመለከቱት በአግባቡ ስለ መፈጸማቸው የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ለምክር ቤቱ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን ስለመለየት

**56. መሰረቱ**

ምክር ቤቱ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ይለያል፡፡

**57. የፍትሐብሔር ጉዳዮች ሀሳቦችን ማመንጨት**

1. ምክር ቤቱ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚታመንባቸውን የፍትሐብሔር ጉዳዮች የሚለያቸው በራሱ አነሳሽነት ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው መንግሥታዊ አካላት በሚቀርብለት አስተያየት መሠረት ሊሆን ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጸ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ባልተጣጣመ ሁኔታ እየተተገበረ ያለ ከሆነ ወይም የጉዳዩ በየክልሉ የተለያየ የአፈጻጸም ተሞክሮ አንድ የጋራ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ለመፍጠር እንቅፋት የሚሆን ከሆነ ወይም ጉዳዩ ከአንድ በላይ ክልሎችን በጋራ የሚመለከት ከሆነ ምክር ቤቱ ይህ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ እንዲወጣለት ያደርጋል፡፡
3. የፌዴሬሽን ምክር ቤትና የክልሎች የጋራ ምክክር መድረክ የፍትሐብሔር ጉዳይ ሃሳቦችን ሊያመነጭ ይችላል፡፡ ምክር ቤቱ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ለመለየት ሌሎች መድረኮችንም ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

**58. የፍትሐብሔር ሕግ ረቂቅ ስለማቅረብ**

1. ምክር ቤቱ አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን የፍትሐብሔር ጉዳዮች በመለየት ሕግ እንዲወጣላቸው ለፌዴራሉ ሕግ አውጪ ያስተላልፋል፡፡
2. የፍትሐብሔር ጉዳዮች አግባብነት ባላቸው መንግሥታዊ አካላት ለምክር ቤቱ የሚቀርብ ከሆነ ከጥያቄው ጋር የሕግ ረቂቅ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

**59. የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ስለማስተላለፍ**

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ተለይቶ የቀረበለትን የፍትሐ ብሔር ጉዳይ በተቻለ ፍጥነት ሕግ ሆኖ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ስምንት

## የፌዴራሉ መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ ስለማዘዝ

### 60. መሠረቱ

ምክር ቤቱ የፌዴራሉ መንግስት በክልሎች ጣልቃ እንዲገባ ያዛል፤

### 61. የፌዴራሉ መንግሥት ጣልቃ ስለሚገባበት ሁኔታ

1. ምክር ቤቱ በአንድ ክልል ውስጥ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ አደጋ ላይ ወድቋል ብሎ ሲያምን የፌዴራሉ መንግሥት ተገቢና ተመጣጣኝ እርምጃ እንዲወስድ ለማዘዝ ይችላል፡፡
2. ምክር ቤቱ ይህንን እርምጃ የሚወስደው አጠቃላይ ሕገ መንግሥታዊ አወቃቀርና የሥልጣን ክፍፍል ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል::
3. በአንድ የክልል መንግስት ተሳትፎ ወይም ዕውቅና ሕገ መንግስቱን ወይም ሕገመንግስታዊ ስርዓቱን ባለማክበር የሚደረግ ድርጊት ውይም እንቅስቃሴ በተለይም፤

   ሀ. በሕገመንግሥቱ እውቅና የተሰጣቸው መንግሥታዊ ተቋሞች ሥራቸውን እንዳያከናወኑ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የተገደቡ እንደሆነ ወይም፣

   ለ. ማንኛውም ክልል በፌዴራሉ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55(16) መሠረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠውን መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ ካቃተው ወይም ለመፈጸም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ወይም፤

   ሐ. በትጥቅ የተደገፈ የአመፅ እንቅስቃሴ ማድረግ ወይም፤

   መ. የፌዴራሉን ሰላምና ፀጥታ ማናጋት ወይም፤

   ሠ. ከሌላ ክልል ወይም ከሌላ ክልል ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ጋር የተፈጠሩ ችግሮችን ሰላማዊ ባልሆነ መንገድ መፍታት ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ ድርጊት ውይም እንቅስቃሴ እንደሆነ ይቆጠራል::

4. ምክር ቤቱ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ አደጋ ላይ የጣለው ሁኔታ ተወግዷል ብሎ ካመነ የፌዴራል መንግሥቱ ጣልቃ ገብነት እንዲያበቃ ሊያዘው ይችላል፡፡
5. የፌዴራል መንግስቱን ጣልቃገብነት ዝርዝር አፈጻጸም አግባብነት ባለው ሕግ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ስለምርጫ ክልል አከላለል እና ስለ ልዩ ውክልና

### 62. የምርጫ ክልሎችን ስለመወሰን

1. በሕገመንግሥቱን አንቀጽ 103 (5) መሠረት ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የምርጫ አከላለልን አስመልክቶ የውሳኔ ሃሳብ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡
2. የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አጠቃላይ አገራዊ ምርጫ ከመካሄዱ ከአንድ ዓመት በፊት የምርጫ ክልሎችን አከላለል ረቂቅ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡
3. ምክር ቤቱ የውሣኔ ሃሳቡን ከማጽደቁ በፊት የውሣኔ ሃሳቡ የሕዝቦችን ሚዛናዊና ተመጣጣኝ ውክልና የማግኘት መብት የሚያስጠብቅ መሆኑን በመመርመር የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ ያጸድቃል፡፡

### 63. ልዩ ውክልና ስለሚሰጣቸው ብሔረሰቦችና ሕዝቦች

1. ምክር ቤቱ የሕዝብ ብዛታቸው አነስተኛ በመሆኑ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተለየ ውክልና የሚያስፈልጋቸው ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ይለያል፤
2. ልዩ ውክልና ስለሚሰጣቸው ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሚለዩበት መስፈርት ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል አስር

## ስለምክር ቤቱ አወቃቀር

### 64. የምክር ቤቱ አደረጃጀት

ምክር ቤቱ አፈጉባዔ፣ ምክትል አፈጉባዔ፣አስተባባሪ ኮሚቴ፣ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች እንዲሁም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

### 65. የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት

1. ምክር ቤቱ በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የራሱ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል፡፡

2. ጽህፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለአፈጉባኤው ነው፡፡

**66. ሕጋዊ ሰውነት**

ምክር ቤቱ የራሱ ሕጋዊ ሰውነት ይኖረዋል፡፡

**67. የምክር ቤቱ አፈጉባዔው ሥልጣንና ተግባር**

አፈጉባዔው፡

1. የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፣
2. የምክር ቤቱን ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣
3. 3 ምክር ቤቱን በሀገር ውስጥ እና በውጪ ይወክላል፣
4. ምክር ቤቱ በአባላቱ ላይ የሚወሰደውን የዲሲፕሊን እርምጃ ያስፈጽማል፣
5. ምክር ቤቱ የሚያስተላልፋቸው ውሣኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣
6. የፌደሬሽን የምክር ቤት በጀት በጽ/ቤቱ ተዘጋጅቶ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲወሰንም ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
7. ሌሎች በሕግ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

**68. የምክር ቤቱ ምክትል አፈጉባዔው  ሥልጣንና ተግባር**

የምክር ቤቱ  ምክትል አፈጉባዔ፣

1. በምክር ቤቱ አፈጉባዔ የሚመራለትን ሥራ ያከናውናል፡፡

2. የምክር ቤቱ አፈጉባዔ በማይኖርበት ጊዜ አፈጉባዔውን ተክቶ ይሰራል፡፡

**69. የምክር ቤቱ ስብሰባና ሥነሥርዓት**

1. ምክር ቤቱ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል፤
2. ምክር ቤት እንዳስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤
3. የምክር ቤቱ ምልዓተ ጉባዔ የሚኖረው ከአባላቱ መካከል ሁለት ሶስተኛው የተገኙ እንደሆነ ነው
4. ምክር ቤቱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በአብላጫ ድምፅ ይሆናል፤

5. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የምክር ቤቱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ዝርዝር በምክር ቤቱ አሰራርና የአባላት የስነምግባር ደንብ የተመለከተው ይሆናል፤

**70. <u>የምክር ቤቱ አባላት አመራረጥ</u>**

1. እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ ሕዝብ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ቢያንስ አንድ ተወካይ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም የብሔር ወይም ብሔረሰቡ አንድ ሚሊዮን ሕዝብ አንድ ተጨማሪ ወኪል ይኖረዋል፤
2. የተወካዮች ብዛት የሚወሰነው የብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝቡ በሃገር ደረጃ በሚኖረው ብዛት መሠረት ነው፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከቱትን መሠረት በማድረግ ምክር ቤቱ ክልሎች መላክ የሚገባቸውን የእያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ ሕዝብ ተወካዮች ብዛት ወስኖ ምርጫ ከመካሄዱ ከአንድ አመት በፊት ለእያንዳንዱ ክልል ያሳውቃል፤
4. የክልል ምክር ቤቶች የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሚልከላቸው የተወካዮች ብዛት መሠረት በምክር ቤቶቹ በራሣቸው ወይም በቀጥታ በሕዝብ እንዲመረጡ በማድረግ የፌዴራል ምክር ቤቶች የጋራ ስብሰባ ከመጀመሩ ከአንድ ወር በፊት ለምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የወኪሎችን ዝርዝር ይልካሉ፡፡
5. ክልሎች የምክር ቤት አባላትን በቀጥታ በሕዝብ ለማስመረጥ ከወሰኑ ምርጫውን አግባብ ባላቸው የምርጫ ሕጎች መሠረት ያከናውናሉ፡፡
6. በምክር ቤቱ የሚወከለው ሕዝብ የራሱ የዞን ወይም የወረዳ መስተዳደር ያለው እንደሆነ ተወካዩ የሚመረጥበት አግባብ ምክር ቤቶቹን ያሳተፈ መሆን ስላለበት ሥርዓቱ በክልል ምክር ቤቶች ሊመቻች ይገባል፡፡
7. የምክር ቤቱ አባላት ምክር ቤቱ ህገመንግስታዊ ተልዕኮዉን እንዲወጣ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው::

**71. <u>የምክር ቤቱ አባላት መብት</u>**

1. ማንኛውም የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባል በማናቸውም የምክር ቤት ስብሰባ ላይ በሚሰጠው አስተያየት ወይም ድምጽ ምክንያት አይከሰስም አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም፡፡
2. ማንኛውም የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፣ በወንጀልም አይከሰስም፡፡

**72. <u>የዲስፕሊን እርምጃ ስለመውሰድ</u>**

አንድ የምክር ቤት አባል የወከለውን ብሔር ብሔረሰብ ሕዝብ በብቃት ሊወክል አልቻለም የሚያሰኝ የዲሲፕሊን ጉድለት ከፈጸመ በምክር ቤቱ አሰራርና የአባላት የስነምግባር ደንብ መሠረት የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

**73· <u>ከምክር ቤት አባልነት ስለመነሣት</u>**

ማንኛውም የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባል ከፈቃዱ ውጪ ከአባልነት ሊነሣ የሚችለው ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ብቻ ነው፡፡

ሀ. በክልል ምክር ቤት የተመረጠ አባል ሲሆን የመረጠው ምክር ቤት እንዲነሣ የወሰነ እንደሆነ

ለ. በቀጥታ በሕዝቡ የተመረጠ አባል ሲሆን ከመራጩ ሕዝብ አስራ አምስት በመቶ (15%) በላይ ሕዝብ የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የይነሣልን ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ

ሐ. የምክር ቤቱ አባል በሚያሳየው የሥነ ምግባር ጉድለት ምክንያት የወከለውን ብሔር፣ ብሔረሰብ ሕዝብ በብቃት ሊወክል አልቻለም በማለት የወከለው የክልል ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲወስን፡፡

**74. <u>ምትክ አባልን ስለመላክ</u>**

1. አንድ የምክር ቤት አባል በሞት ወይም ከዚህ በላይ በአንቀጽ 73 በተመለከቱት ምክንያቶች ወይም በራሱ ፈቃድ ከአባልነት የተነሣ እንደሆነ ምክር ቤቱ ጉዳዩን ለሚመለከተው ክልል ያሳውቃል፡፡
2. የክልል ምክር ቤቱም ውሣኔው በደረሰው በአጭር ጊዜ ውስጥ ምትክ ተወካዩን በራሱ በመምረጥ ወይም በቀጥታ በሕዝብ እንዲመረጥ በማድረግ ይልካል፡፡

<u>**ክፍል አስራ አንድ**</u>

<u>**ስለ ኮሚቴዎች**</u>

**75. <u>ኮሚቴዎችን ስለማቋቋም</u>**

1. ምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባሩን በብቃት ለመወጣት የምክር ቤቱ አባላት የሚገኙባቸው ቋሚ እና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡፡ የሥራ ኃላፊነታቸውንም ይወስናል፡፡
2. እያንዳንዱ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ፀሐፊ ይኖረዋል፡፡
3. ምክር ቤቱ ከእያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ እስከ ሶስት አባላት በምክር ቤቱ በቋሚነት እንዲሰሩ ማድረግ ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከእያንዳንዱ ኮሚቴ በቋሚነት የሚሰሩ አባላት ቁጥር እንዲጨምር ማድረግ ይችላል፡፡

**76. <u>ስለኮሚቴ አመራሮች ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. የኮሚቴው ሰብሳቢ፤

ሀ. የኮሚቴውን ስብሰባ የመጥራትና የመምራት

ለ. ለኮሚቴው መደበኛ ስብሰባዎች የሚቀርቡትን ጉዳዮች አጀንዳዎችን የመቅረጽ፣

ሐ. ምልዓተ ጉባዔ መኖሩን የማረጋገጥ

መ. የኮሚቴው ውሣኔዎች ወደ ሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፉ የማድረግ

ሠ. የኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ እና የሥራ ክንውን ሪፖርት በየወቅቱ ለምክር ቤቱ የማቅረብ ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

**2. <u>የኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ</u>**

ሀ. የኮሚቴው ሰብሳቢ ሳይኖር ሰብሳቢውን ተክቶ የመሥራት

ለ. በኮሚቴው ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የመፈፀም ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

**3. <u>የኮሚቴው ፀሐፊ</u>**

ሀ. የኮሚቴውን ቃለ ጉባዔዎች ይይዛል፣ ያደራጃል ሰነዶች በቅደም ተከተል ተመዝግበው መያዛቸውንና መቀመጣቸውን ያረጋግጣል፣

ለ. ለኮሚቴው የሚቀርቡትን አቤቱታዎች፣ የውሳኔ ሀሳቦችና እና ማናቸውም ለምክር ቤቱ የሚቀርቡ ጉዳዮችን በሥርዓት አደራጅቶ ለኮሚቴው አባላት እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡

ሐ. በኮሚቴው ወይም በሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ይፈጽማል፡፡

**77. <u>ምልዓተ ጉባዔ</u>**

1. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
2. ምክር ቤቱ ሌላ ደንብ ካላወጣ በቀር የኮሚቴ ውሣኔ የሚተላለፈው በአብላጫ ድምጽ ይሆናል፡፡
3. ድምጽ እኩል በእኩል በሚከፈልበት ጊዜ ሰብሳቢው የሚደግፈው አቋም የኮሚቴው የመጨረሻ ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሀሳብ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አስራ ሁለት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**78. <u>ስለ ክትትል</u>**

ምክር ቤቱ የሰጠው ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በሚመለከታቸው አካላት መፈጸማቸው በሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች አማካይነት ክትትል እየተደረገ ሪፖርት መቅረብ አለበት፡፡

**79. ስለበጀት**

1. የምክር ቤቱ በጀት

   ሀ. በመንግሥት ከሚመደብ በጀት

   ለ. ከስጦታና እርዳታ

   ሐ. ከማንኛውም ሌላ ሕጋዊ ምንጭ የተውጣጣ ይሆናል

2. ምክር ቤቱ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 65 መሰረት በጀቱን በቀጥታ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ ያስወስናል፡፡
3. የምክር ቤቱ በጀት ዝግጅትና የአቀራረብ ሒደት በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ገቢ በምክር ቤቱ የባንክ ሂሳብ ተቀምጦ የምክር ቤቱን ሥራ ለማከናወን ብቻ ይውላል፡፡
5. ምክር ቤቱ የበጀት አጠቃቀሙን የሚያሣይ ትክክለኛ የሂሣብ ሰነድ መያዝ ይኖርበታል፡፡
6. የምክር ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና የገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

**80. የውሣኔው የመጨረሻነት ባህርይ፣ ደረጃና አስገዳጅነት**

1. የፌደሬሽን ምክር ቤት በቀረበለት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል፣
2. ምክር ቤቱ የሚሰጣቸው ሕገመንግስታዊ ዉሳኔዎች የሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ ክብደት ደረጃም ይኖራቸዋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ውሳኔው መሰረታዊ የሕገመንግስታዊ ትርጉም ስህተት እንዳለበት የሚመለከታቸው አካላትን በማማከር አፈጉባኤው ካመነበት ጉዳዩ በድጋሚ ለምክር ቤቱ ለውይይት ሊቀርብ ይችላል፡፡
4. ማንኛውም ሰው፣ የፌደራልና የክልል ፍርድ ቤቶች፣ የፌዴራልና የክልል መንግስታት፣ የመንግስት ባለሥልጣናት ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት የምክር ቤቱን ውሣኔ የማክበር፣ የማስፈጸምና የመፈፀም ግዴታ ይኖርበታል፡፡

**81. የሕግ ረቂቅ የማቅረብ ሥልጣን**

ምክር ቤቱ በሥልጣኑ ክልል በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሕግ ረቂቅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የማቅረብ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

**82. ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባራት ለማከናወን ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ ለማውጣት ይችላል፡፡

**83. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

አስተባባሪ ኮሚቴው ይህን አዋጅ ወይም ምክርቤቱ የሚያወጣውን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

**84. የተሻሩ ሕጎች**

1. አዋጅ ቁጥር 251/1993 ዓ.ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ውሣኔዎችና አሰራሮች በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

**85. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ........ቀን 2013 ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዚዳንት**